

# በኮሎምብያ ዲስትሪክት የተማሪዎች ሥነ-ምግባር መመሪያ

## ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የሚያገለግል መመሪያ



OFFICE OF THE STUDENT ADVOCATE


DC Office of the Ombudsman for Public Education

ከ 'Every Student Every Day' ጋር በትብብር የተዘጋጀ

EVERY STUDENT EVERY DAY

Ending DC's School-to-Prison Pipeline

ስለተማሪው የሥነምግባር ችግር ትምህርት ቤቱ ማስጠንቀቂያ ከላከ በኋላ፣ አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቦች፣ የብቸኝነት ስሜት እና የሚቀጥለውን እርምጃ እንዴት መውሰድ እንዳለባቸው ለማወቅ የሚይዙት የሚጨብጡት ሊጠፋቸው ይችላል፡




የትምህርት ቤታችሁ የስነምግባር ፖሊሲው “የተማሪዎች አግባብ ያለው ትምህርት ቤት ማግኘት የተስተካከለ ድንጋጌ“ (Students Fair Access to School Amendment Act)ን የተከተለ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የዲሲ እና የፌደራል ሕጎችን ተከትሎ መስራቱን ማረጋገጥ አለበት። የስነምግባር ፖሊሲው፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ተማክረው የቀረጹት እና የትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽን ጨምሮ ለሕዝብ በይፋ የቀረበ መሆን አለበት።.

*የትምህርት ቤትዎ የስነምግባር ፖሊሲ ከአዲሱ ሕግ ጋር የተመጣጠነ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ በኦንላይን ወይም በትምህርት ቤቱ የእንግዳ መቀበያ አካባቢ ታትሞ የሚገኘውን የትምህርት ቤትዎን መመሪያ ይመልከቱ*

በ2018 የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ካውንስል "የተማሪዎች አግባብ ያለው ትምህርት ቤት ማግኘት የተስተካከለ ድንጋጌ" (Students Fair Access to School Amendment Act)ን አሳለፈ።

ይህ ለተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች የተዘጋጀ መመሪያ፣ በዲሲ ሕግ መሠረት ሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መከተል የሚገባቸውን የትምህርት ቤት ስነምግባር አዳዲስ ደንቦችን ያብራራል።

# ማውጫ


የትምህርት ቤት ስነምግባር ሕግ.......................................................................... ገጽ 2

ማወቅ የሚጋባዎ አባባሎች፡ አንድወጥ ሕጋዊ ትርጓሜ ................................................ ገጽ 3

መብቶችዎን ይወቁ፡ በስነምግባር ምክንያት የማስወገጃ የተወሰነ የጊዜ ገደቦች ............ ገጽ 4

መብቶችዎን ይወቁ፡ ተማሪውን እንዳይገለል የሚያደርገው ጥበቃዎች.......................... ገጽ 5

መብቶችዎን ይወቁ፡ በሚገለልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ትምህርት ማግኘት..................... ገጽ 6

አማራጭ የስነምግባር ምላሾች.......................................................................... ገጽ 7

ከተማሪዎች ስነምግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶችእናቢሮዎች ........ ገጽ 8

የእራስ መከራከር...................................................................................... ገጽ 10

ውይይትን አነሳሾች፡ የሚጠየቁ ጥያቄዎች............................................................ ገጽ11

ማወቅ የሚጋባዎ አባባሎች፡ አጠቃላይ አባባሎች....................................................... ገጽ 12

ማወቅ የሚገባዎ ቁጥሮች.........................................................በመጨረሻው የገጽ ሽፋን

# የትምህርት ቤት የስነምግባር ሕግ

## የ2018 የተማሪዎች አግባብ ያለው ትምህርት ቤት ማግኘት የተስተካከለ ድንጋጌ

- እገዳው አስጊ የሆነ የደህንነት አደጋ ባስከተለ ክስተት ስካልሆነ ድረስ፣ ከትምህርት ቤት በኋላ ያሉ እንቅስቃሴዎች ላይ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማገድን መቀነስ
- በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጸሙ አነስተኛ የጥፋት ድርጊቶችን ላይ የእገዳ እርምጃ መውሰድን ማቀብ
- ከታገደም፣ ይህ ሕግ የልጁ ከትምህርት መስጫው ግቢ ውጪ ትምህርት የማግኘት እና ወደ መደበኛ ክፍሉ በተሳካ ሁኔታ እንዲመለስ ዕቅድ የማውጣት መብቱን ይጠብቅለታል።

ድንጋጌውን በሙሉ ለመመልከት ይህንን ሊንክ (link) ይከተሉ https://code.dccouncil.us/dc/council/laws/22-157.html

**ኦውገስት (ነሐሴ) 25 ቀን 2018**

የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች ከአዲሱ ሕግ ጋር መስማማት አለባቸው።

**SY2019-2020**

ውስን የሆነ የማግለል የስነምግባር ቅጣት በአንደኛ/መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ይውላል

**SY2020-2021**

ውስን የሆነ የማግለል የስነምግባር ቅጣት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ይውላል

## ትምህርት ቤቶች ማድረግ የሚችሉት

- ጥቃትን የተጠቀመን ተማሪ ማገድ
- በስነምግባር ምክንያቶች የአደጋ ሁኔታዎች በሚፈጠሩ ጊዜ፣ ለቀሪው የቀኑ የትምህርት ክፍለጊዜ ተማሪውን ማገድ
- በስነምግባር እና በቀለም ትምህርት ምክንያቶች፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጪ እንቅስቃሴዎች (እንደ አትሌቲክስ ከመሳሰሉት) ማገድ

## ትምህርት ቤቶች ማድረግ የማይችሉት

- የpre-Kተማሪዎችን ማገድ
- ትምህርት ቤት ለመምጣት ያልቻለን ተማሪ ማገድ ወይም ማስወጣት
- ተማሪው ከትምህርት ቤት ከወጣ በኋላ፣ እንዲመለስ ለማድረግ ወላጆች ከተማሪው ጋር እንዲመጣ ወይም ኮንፈረንስ እንዲካፈል መጠየቅ
- ለK-5ክፍሎች፣ ከአምስት ተከታታይ ቀናት በላይ፤ እንዲሁም ከ6-12 ክፍሎች ለአስር ተከታታይ የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት አስወጥቶ ማገድ
- በእገዳው ወቅት ተማሪው ከቀለም ትምህርት እንቅስቃሴዎች ማገድ ወይም ለእድገት ወይም ለምረቃ ማግኘት ከሚችለው ክሬዲት መከልከል



ተማሪው ልዩ እንክብካቤ የሚፈልግ ተማሪ ከሆነ፣ እዚህ በመመሪያው ዝርዝር ውስጥ ከተዘረዘሩት ተጨማሪ መብቶች አሉ። ምንም ምን እንደሆኑ እዚህ ይመልከቱ፡ https://sboe.dc.gov/node/1153932

# ማወቅ የሚገባዎ አባባሎች

## አንድወጥ የስነምግባር ሕጋዊ ትርጓሜ....

በሁሉም LEA በወጥነት እንዲያገለግሉ በርካታ አባባሎችን ሕጉ ይተረጉማቸዋል፡

- <u>ሆን ብሎ አለመታዘዝ፡</u> የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ማስተጓጎል ወይም በትክክል ስልጣን የተሠጠውን የትምህርት ቤቱን ሠራተኛ ሆን ብሎ መቃወም።

- <u>በትምህርት ቤት ውስጥ እንዳለ እገዳ፡</u> በስነምግባር ቅጣት ምክንያት፣ ከሚማርበት ክፍል በጊዜያዊነት ማስወጣት።

- <u>የረጅም ጊዜ እገዳ፡</u> በስነምግባር ቅጣት ምክንያት፣ ከ6 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት በጊዜያዊነት ማስወጣት።

- <u>ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ፡</u> ከትምህርት ቤት ቀናት በከፊል፣ እና "ያለፈቃዳቸው መባረሮችን" ጨምሮ፣ በስነምግባር ቅጣት ምክንያት ከትምህርት ቤት ማስወጣት።

- <u>ያለፈቃዳቸው ማባረር፡</u> ከግማሽ የትምህርት ቀኑ ባነሰ፣ ከትምህርት ቤት ማስወጣት።

- <u>የአደጋ ጊዜ ማስወጣት፡</u> በስነምግባር ምክንያት ተማሪው ሌሎች ተማሪዎች እና ሠራተኞች ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ትምህርት ቤቱ ካመነ፣ ወዲያውኑ ከትምህርት ቤቱ ማስወጣት ወይም ትምህርት ቤት እንዳይመለስ ያደርጋል።

- <u>ያለፈቃዳቸው መዛወር፡</u> ለቀሪው የትምህርት ዓመት ወይም ከዚያ ለበለጠ ጊዜ፣ ተማሪው ከአንድ ትምህርት ቤት ወደሌላኛው በስነምግባር ምክንያት ማስወጣት።

- <u>በግድ ማስወጣት፡</u> በስነምግባር ምክንያት፣ ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ላልተወሰነ ጊዜ ማስወጣት።

# መብቶችዎን ይወቁ

በስነምግባር ቅጣት መባረሮች፣ የቅጣት የጊዜ መጠን ገደቦች

## ክፍሎች:
## ከወዋዕለ ሕፃናት - 5ተኛ

እያንዳንዱ እገዳ ከ

**5**

ተከታታይ የትምህርት ቀናት ሊበልጥ አይችልም

## ክፍሎች:
## ከ6ተኛ - 12ተኛ

እያንዳንዱ እገዳ ከ

**10**

ተከታታይ የትምህርት ቀናት ሊበልጥ አይችልም

## ክፍሎች:
## ሁሉም

አጠቃላይ እገዳው በድምሩ ከ

**20**

የትምህርት ቀናት ሊበልጥ አይችልም*

*የLEA ዋና መሪው፣ እገዳው ከ20 ቀናት በላይ መሆኑ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስለመገኘቱ ወይም የተማሪው ባህሪይ አደገኛ ሁኔታ ስለነበረው የወጣ ለመሆኑ የፅሁፍ ማረጋገጫ ካላቀረበ በስተቀር

## ከትምህርት ገበ ታ መ ገኘት - ጋር የ ተ ያ ያ ዘ ስነምግባር

ተ ማ ሪዎች በትምህርት ገበ ታ ባ ለ መ ገ ኘ ታቸው ምክንያት ሊ ታ ገ ዱ ወይም ሊ ወ ጡ አይችሉም ። ሆኖም ግን፣ ተ ማሪው ለ20 ተ ከ ታታይ ቀናል ከ ቀ ረ እ ና ለ ሚ ቀ ረበት ምክንያት ፈቃድ ካ ላ ገኘ፣ ተ ማ ሪ ው ከትምህርት ቤት ምዝ ገ ባ ይ ወጣል ።

ትምህርት ቤ ቱ ፣ ከትምህርት ቤት ማገድን፣ በግድ ማስ ወጣን ወይም ያ ለ ፈ ቃ ዳቸው ማ ዛወር ን ፣ ፈቃድ ሳይ ሰጠው ከትምህርት ገበታው እን ደ ቀ ረ ወይም እን ደ አ ረ ፈ ደ ተደር ጎ መ ቁጠር የ ለበትም ።

## ከ መ ዋ ዕ ለ ሕ ፃናት እስ ከ 8 ክፍሎች የስነምግባር ማግለል ቅጣት ገ ደቦች

የ ተ ማሪው ባ ህሪይ በደህንነት ላይ ወይም ስሜትን የ ሚ ያ ስጨንቅ ስ ጋ ት እስ ካ ላ ደ ረ ሰ ጊ ዜ ድረስ፣ ከትምህርት ቤት ማገድን፣ በግድ ማስ ወጣን ወይም ያ ለ ፈ ቃ ዳቸው ማ ዛወር ን ፣ ትምህርት ቤ ቱ ሊ ጠቀም አይችልም ።

## ከ9 እስ ከ 12 ክፍሎች የስነምግባር ማግለል ቅጣት ገ ደቦች

ትምህር ት ቤቶች ፤ ከትምህርት ቤት ማገድን፣ በግድ ማስ ወጣን ወይም ያ ለ ፈ ቃ ዳቸው ማ ዛወር ን ፣ ለ ሚ ከ ተሉት መ ጠቀም ይችልም፡

- የአ ለ ባበስ ደን ብ መጣስ
- ሆን ብ ሎ አ ለ መ ታዘዝ፣ አ ለማክበር፣ ወይም አ ለ መ ታዘዝ
- ከትምህርት ገበ ታ ው ጪ ና ከትምህርት ቤ ቱ ቅጥር ጊ ቢ ው ጪ ሆ ኖ ከትምህርት ቤ ቱ እንቅስ ቃ ሴዎች ጋር ተ ያያዥነት የ ሌለው ( የ ተ ማሪው ባ ህ ሪ ይ ለደህንነት ወይም ስሜትን አ ስ ጨ ና ቂ የ ሆ ነ ስጋት የ ሚፈጥር ሆ ኖ እ ስካል ተ ገ ኘ ድረስ )

የገንዘብ እ ር ዳ ታ ካ ገኘ፣ ከSY2019 -20 በ ሥ ራ ላይ ይውላል ።

የገንዘብ እር ዳ ታ ካ ገኘ፣ ከSY2020 -21 በ ሥ ራ ላይ ይውላል ።

# መብቶ ችዎን ይ ወ ቁ

ተ ማ ሪዎ ችን ከማግለል ጥ በ ቃ ን በ ተ ከ ተ ለ ሁ ኔ ታ ፤ ጥቃት የማድረስ ባ ህሪይ የ ሌ ላቸውን የማስ ወጣት ተግ ባሮ ችን ፣ ማ ሳ ጠ ር እ ና ማቆም

## ከትምህርት ቤት ው ጪ የማግለል ቅጣት ገደብ

በአንድ የትምህርት ዓመት በጠቅ ላ ላ ድም ሩ ከ20 ቀናት በላይ ለ ሆ ነ ጊ ዜ ተ ማ ሪዎች መ ታገድ የ ለ ባቸውም ። የLEA ዋ ና መሪው ፣ የ ተ ማሪው ባ ህ ሪ ይ አ ደ ገ ኛ ሁ ኔ ታ በ መ ሆ ኑ ምክንያት እን ደ ሆ ነ የ ሚ ያሳይ የ ፅሁፍ ማ ረ ጋ ገ ጫ ለ ተ ማሪው እ ና ለ ወ ላ ጆ ቹ ካ ሰ የ ብ ቻ ተ ቀባይነት ይ ኖ ረዋል ።

## አን ደ ኛ ደ ረ ጃ ትምህርት ቤ ት ን ፣ ከትምህርት ቤት ው ጪ የ ሚ ያደርግ የእ ገ ዳ ቅጣት ገ ደ ብ

ተ ማሪው ከ መ ዋ ዕ ለ ሕ ፃናት እስ ከ 5 ተ ኛ ክፍል ከ ሆነ፣ እያንዳን ዱ የትምህርት ቤት የ ሚ ወገድበት ቅጣት ከ5 ተ ከ ታታይ የትምህርት ቀናት ሊበል ጥ አይችል ም ።

## ለ መ ካ ከ ለ ኛ እ ና ከፍ ተ ኛ ደ ረ ጃ ትምህርት ቤት፣ ከትምህርት ቤት ው ጪ የ ሚ ያደርግ የእ ገ ዳ ቅጣት ገ ደ ብ

ተ ማሪው ከ 6 ተ ኛ እስ ከ 12 ተ ኛ ክፍል ከ ሆነ፣ እያንዳን ዱ የትምህርት ቤት የ ሚ ወገድበት ቅጣት ከ10 ተ ከ ታታይ የትምህርት ቀናት ሊበል ጥ አይችል ም ።

# መብቶችዎን ይወቁ

## በተገለሉበት የጊዜ ገደብ ውስጥ የትምህርት እድል ማግኘት

ከትምህርት ቤት ውጪ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥም እያለ ለሚታገዱ ማንኛውም ተማሪዎች፣ ትምህርታቸው የሚቀጥልበትን አጠቃላይ ዕቅድን ትምህርት ቤቱ ማውጣት አለበት። ዕቅዱ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት በሚያሟላ ሁኔታ ሊስተካከል ይችላል፤ ነገር ግን ተማሪው የሚከተሉት ማግኘት አለበት፡

በእገዳው ወቅት ሁሉንም ተገቢ የቤት ስራዎች ማግኘት መቀጠል አለበት።

በእገዳው ጊዜ ያመለጡትን የትምህርት ቤት ስራዎችን (ፈተናዎችን ጨምሮ) በሌላ ጊዜ መውሰድ ይችላል።

ትምህርት ነክ ስራዎችን በተመለከተ ከትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል።

### የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች፡

- ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች FAPE ማግኘት የመቀጠል መብት አላቸው፤ ይኸውም ልዩ የሆነ የትምህርት አሰጣት እና የተያያዙ አገልግሎቶችን በእገዳው ጊዜ ማግኘትን ይጨምራል።
- የአካል ጉዳይ ያላቸው ተማሪዎች፣ ከጉዳተኝነታቸው በተያያዘ አካሄድ መሠረት ከ10 ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት መገለል የለባቸውም። ከተማሪው ጉዳተኝነት ጋር የባህሪው አቀራረብ ለውጥ ያስከተለበትን መወሰኛ (የተማሪው ጉዳተኝነት እና በይፋ ከሚያሳየው ባህሪይ ጋር በተያያዘ ለስነምግባር ድርጊቱ አስተዋፅዖ ያደረገውን ነገር ግንኙነት ለመገምገም) ትምህርት ቤቱ እና ቤተሰቦች በጋራ ይሰራሉ።

ስለትምህርት ቤቱ ልዩ ቀጣይነት ያላቸው የምትህርት ዕቅድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የትምህርት ቤትዎን የመመሪያመጽሐፍ/የተማሪዎች ስነምግባር ፖሊሲን ይመልከቱ።


# አማራጭ የሆኑ የስነምግባር ምላሾች

ወደተከሰተው እውነተኛው ጉዳይ ቀርቦ መንስዔውን እና ከስር መሠረቱ መነጋገርን በጨመርን ቁጥር፣ የበለጠ ይሰራል። በቤት ውስጥ እና/ወይም ትምህርት ቤታችሁን ለመጠየቅ ግንዛቤ ልትሰጡዋቸው የምትችሏቸው አማራጭ የስነምግባር ምላሾች የሚከተሉት ናቸው፡

- ምላሽ ሰጪ ፍትህ (በገዛ ድርጊቶቻቸው የተጎዱን መፍትሄ በጋራ መፈለግ እና መርዳት) መለስ ተብለው የሚደረጉ ውይይቶች፣ የዙሪያ ውይይቶች እና ኮንፈረንሶች ወይም መሐል በአቻነት የሚያቀርብ ማግባባቶች
- የፅሁፍ የሐሳብ ማፍለቂያ እና የይቅርታ ጥያቄ
- በትምህርት ቤት ወይም በመኖሪያ ቤት ልዩ መብትን ማጣት
- የእንክብካቤ ሰጪ እና የተማሪ/አስተማሪ ኮንፈረንስ
- የማህበረሰብ አገልግሎት
- የጊዜ ሰሌዳ ማስተካከል
- የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ
- ለተጨማሪ እርዳታ ማህበረሰብን ማዕከል ወደ አደረገ ድርጅት መላክ
- ከትምህርት ቤቱ የባህሪይ ጤና አገልግሎት ሰጪ ጋር መነጋገር
- በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ውጪ ጠቃሚ ምክር ሰጪ ፕሮግርም
- በትምህርት ቤት ውስጥ በየቀኑ/በሳምንት በተማሪው እና በአዋቂ ጠቃሚ ምክር ሰጪ መካከል ክትትል ማድረድ
- በተማሪው እና አስተማሪው መካከል የባህሪይ ኮንትራት/ፕላን ማድረግ

ምላሽ ሰጪ የፍትህ ልምድ እና አማራጭ ምላሾችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ከፈለጉ https://osse.dc.gov/page/restorative-justice-trainings-and-resources ይጎብኙ።

# መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች እና ቢሮዎች




**የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ካውንስል:** የዲሲ ካውንስል የDCPS እና ቻርተር ትምህርት ቤቶችን የሚያስተዳድር ሕጎችን ጨምሮ ለከተማው ሕጎችን ይቀርፃል ያሳልፋል።

**የትምህርት ኮሚቴ:** ይህ ኮሚቴ በዲስትሪክቱ ውስጥ ከትምህርት ጋር የተያያዙ ሕጎችን እና ድርጊቶችን በበላይነት የሚመለከት እና ለትምህርት ድርጅቶች በጀትን የሚፈቅድ ሕጎችን መዳሰስ እና እንዲታዩ አስተያየት ያቀርባል።

**የስቴት የትምህርት ቦርድ:** የስቴት ቦርዱ፣ በስቴት ደረጃ ያሉ የትምህርት ፖሊሲዎችን ያጸድቃል፤ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪን ያማክራል።

**የተማሪዎች ተከራካሪ ቢሮ:** የተማሪዎች ተከራካሪ ቢሮ፣ በወላጆች ትምህርት፣ አንድለአንድ የምክር አገልግሎት፣ እርዳታ የማግኛ ምንጮችን አንድ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ይረዳል።

**የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እምባጠባቂ ቢሮ :** የእንባ ጠባቂ ቢሮ፣ ዓድልዎ የሌለበት እና ለብቻው የተቋቋመ ቢሮ ሆኖ፣ ቤተሰቦች እና ትምህርት ቤቶች አማራጭነት ባለው ግጭት ማስወገኛ ሂደት ጉዳዮቻቸውን እና አቤቱታቸው እንዲፈቱ ይረዳል።

**የትምህርት ምክትል ከንቲባ:** የትምህርት ምክትል ከንቲባ፣ በከንቲባው የትምህርት ራዕይ ላይ ተመርኩዞ፣ ፖሊሲዎችን ያዘጋጃል፣ ያቅዳል እንዲሁም ያስፈጽማል።

**የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ:** በሌሎች ስቴቶች እንዳለው የትምህርት መምሪያ በተመሳሳይነት፣ OSSE በዲሲ የስቴት የትምህርት ድርጅት (SEA) ነው። OSSE፣ DCPSን እና ቻርተር ትምህርት ቤቶችን የዲሲ የፌደራል የትምህርት ሕጎች እና ፖሊሲዎች መከተላቸውን ይከታተላል።

**የአካባቢ የትምህርት ድርጅቶች:** በሌሎች ስቴቶች የትምህርት ዲስትሪክቶች እንዳለው ሁሉ፣ በLEA አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይቆጣጠራል። DCPSም LEA በመሆኑ እና እያንዳንዱ ቻርተር ኔትወርኮችም የራሱ LEA ነው። እያንዳንዱ LEA የራሱ የሆነ ፖሊሲን በመቅረጽ እና የፌደራል እና ስቴት ፖሊሲዎች በመተግበር ይቆጣጠራል።

# ከተማሪ ስነምግባር ጋር የተገናኘ

**ይህ በምዕፃረ ቃል የተፃፈ የሥልጣን ካርታ የሕዝብ ትምህርት ስልጣንን እና አገልግሎትን በግልፅነት እንደተጨማሪ የመከራከሪያ መሣሪያነት ለመጠቀም ታስቦ የተዘጋጀ ነው።**

**እዚህ የተገለጹት ድርጅቶች እና ቢሮዎች ዝርዝር አድራሻ ከዚህ መመሪያ የጀርባ ሽፋን ላይ ይገኛል።**

የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ምክትል ከንቲባ

የከንቲባው ባለሥልጣን ቢሮ

የስነምግባር ጤና መምሪያ

የልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት

የአፍሪካን አሜሪካን ጉዳይ ቢሮ

የአባቶች፣ ጎልማሶች እና ወንዶች ኮሚሽን

የውስጥ አገልግሎቶች

አስተዳደራዊ ጉዳይ ሰሚ ቢሮ

**ከንቲባ፡** የከንቲባው ቢሮ የተለመደውን የሕዝብ ትምህርት ቤት ዘዴን (DCPS) ይቆጣጠራል። የDCPSን ቻንስለር እና የትምህርት ምክትል ከንቲባን ይሾማል።

**የከተማ አስተዳደር፡** እንደከንቲባ ተሿሚነቱ፣ የከተማ አስተዳደር፣ DCPSን እና ሌሎችም በተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ትምህርት ቤቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ በሁሉንም አስፈፃሚ ድርጅቶች የእለት-ተዕለት እንቅስቃሴን በበላይ ይከታተላል።

**የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ምክትል ከንቲባ፡** የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ምክትል ከንቲባ፣ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች በትምህርት ቤት የጤና ፕሮግራሞችን በሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፕሮግራሞችን በመርዳት እና በቤትአልባነት የሚሰቃዩ ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን እርዳታ በመስጠት ያገለግላል።

**የስነምግባር ጤና መምሪያ፡** የስነምግባር ጤና መምሪያ የትምህርት ቤቱን የአምዕሮ ጤና ፕሮግራምን ያካሂዳል። ለሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች እና አስተማሪዎች በስነምግባር ጤና እና ነፍስን በገዛ እጅ ማጥፋትን ለመከላከል ስልጠና ይሰጣል።

**ልጅ እና ቤተሰብ አገልግሎቶች ድርጅት፡** ይህ ድርጅት በዲስትሪክቱ የሚገኝ የልጅ በመልካም ሁኔታ መገኘት እና ደህንነት ጠባቂ ድርጅት ነው። CFSA የልጁን ደህንነት በቀረበው አቤቱታ መሠረት የደረሰን ጥቃት እና ቸልተኝነት ያጣራል፤ ከቤተሰቦችም ጋር በመስራት የቤት ውስጥ ሁኔታዎችን እንዲሻሻሉ ያደርጋል። ከትምህርት ዘዴ ጋር አብሮ በመስራት፣ በDCPS እና ቻርተር ትምህርት ቤት የሚገኙ አስተማሪዎች እና አስተዳዳሪዎች እንዴት በደል/ማጎሳቆልን ሪፖርት እንደሚያደርጉ ስልጠና ይሰጣል።

**የአፍሪካን አሜሪካን ጉዳዮች ቢሮ፡** በዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችን በመንግስት የእርዳታ ምንጮች እና አገልግሎቶች፣ በፕሮግራም ከተቀናጀ እርዳታ ጎን ለጎን በማካሄድ በቂ እውቀት እንዲያገኙና በሙሉ ስልጣን ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል።

**የአባቶች፣ ጎልማሶች እና ወንዶች ኮሚሽን፡** የአባቶች፣ ጎልማሶች እና ወንዶች ኮሚሽን፣ በዲሲ ውስጥ በስፋት ያልተዳረሰውን ማህበረሰብ፣ አባት አልባነትን እና ዓድልዎ የሌለበት ትምህርት የተመለከተ ጉዳይን ለከንቲባው እንደ አማካሪ ቡድን በመሆን ያገለግላል።

**አስተዳደራዊ ጉዳይ ሰሚ ቢሮ፡** አስተዳደራዊ ጉዳይ ሰሚ ቢሮ፣ በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተወሰኑ ስነምግባር ድርጊቶችን ያካተተ ተሰሚነትን ያካሂዳል። ለምሳሌነት ከተካተቱት ውስጥ በDCPS ለTier IV ወይም V ማገጃ ወይም ማግለል ላይ አስተያየቶችን መስጠትን ይጨምራል።

**የሕዝብ ደህንነት እና ፍትህ ምክትል ከንቲባ፡** የሕዝብ ደህንነት እና ፍትህ ምክትል ከንቲባ የሕዝብ ደህንነትን እና ሕግ ማስከበሪያ ድርጅቶችን የሚያቀናብር እና የሚረዳ ነው።

**የዲሲ ብሔራዊ ጥበቃ፡** የዲሲ ብሔራዊ ጥበቃ ከOSSE ጋር በመተባበር፣ የካፒታል አሳዳጊ ወጣት አስቸጋሪ/ፈታኝ ሁኔታዎች አካዳሚ (Capital Guardian Youth Challenge Academy) (ለዲሲ ተማሪዎች፤ ወታደራዊ ስልት፣ መኖሪያ፣ ሁለተኛ እድል ሰጪ ፕሮግራም) ያካሂዳል።

**የተጠቂዎች አገልግሎት ቢሮ እና የፍትህ ልገሳዎች፡** በዲሲ የሕዝብ ደህንነትን ለማሻሻል ግዳጅ ያለበት ይህ ቢሮ የ'Show Up, Stand Out' ፕሮግራምን የሚያካሂድ (ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት አዘውትረው እና በሰዓቱ እንዲያመጡ እርዳታ የሚሰጥ)


**የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ፡** የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በስራ ቦታ እና በትምህርት ቤቶች ዓድልዎን ለማስወገድ ይሰራል። OHR በተጨማሪም፣ የማንጓጠጥ ሪፖርትን የሚመረምር እና የማንጓጠጥ ሰለባ የሆኑ ተማሪዎችን ዳግም መረጋጋትን እንዲገነቡ የሚሰራ የወጣት ከተማ-አቀፍ አንጓጣጭነትን መከላከል ፕሮግራምን ያቀፋል።

**የወጣቶች መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች መምሪያ፡** የወጣቶች መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች መምሪያ፣ በወንጀል የተከሰሱ እና በDYRS ተቋም የታቀፉ፣ እንዲሁም በሆነ ወንጀል ለፍርድ ለመቅረብ እየተጠባበቁ ያሉ ልጆችን የሚከታተል እና የሚንከባከብ ነው። በDYRS ተቋም የሚገኙ ተማሪዎች ልክ እንደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ሁሉ አንድ ዓይነት ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።

# ለእራስ መከራከር

## እነማን ማን ናቸው፡ እርዳታን የት ማግኘት እንደሚችሉ ይለዩ

ሁሉም በዲስትሪክቱ የሚገኝ LEA፣ ትምህርት ቤት እንዴት እንደሚካሄድ የራሱ የሆነ ቅንጅት እና ሞዴሎች አሉት - ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ፣ ለተማሪዎች ስነምግባር ኃላፊነት የሚወስዱ ሠራተኞች እና ማዕከላዊ የሆነ የቢሮ አመራር አለው። በዚህ አሰራር ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት፣ የተማሪዎች የመመሪያ መጽሐፍዎን ይመልከቱ።*




እዚህ ይጀምሩ

ይህ በDCPS ውስጥ ከየት እንደሚጀምሩ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

*ለሕዝብ ቻርተር የመመሪያ መጽሐፍን በዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ በኩል “"Find a Charter School" የሚለውን በመጠቀም ማግኘት ይቻላል።
ይህንን ሊንክ (link) በመከተል ያግኙ፡

Find a Charter School

www.dcpcsb.org/find-a-school

የተወሰኑ ባህሪያቶች ወይም ጥሰቶች፣ ተጋግለው ተማሪዎች መደበኛ ወደሆነ ፍርድ ቤት ሊመራው ይችላል። በDCPS ውስጥ ከሆነ፣ በአስተዳደራዊ ጉዳይ ሰሚ ቢሮ ውስጥ ይሆናል። በቻርተር ከሆነ ደግሞ፣ ከበላይ የLEA ሠራተኞ ጋር የመሆን እድሉ የሰፋ ነው።

በነዚህ ሁኔታዎች ወቅት፣ መብቶችዎን በሚገባ እንዲያውቁ፣ የሂደቱን ዝርዝር፣ እና እርዳታን እንዲጠይቁ እናበረታታለን።
በርካታ የማህበረሰብ እርዳታ ምንጮች በዚህ መመሪያ የጀርባ ገጽ ይገኛሉ።

# ውይይት አነሳሾች

## የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### እራስዎን ይጠይቁ

- በትምህርት ቤት ወይም በአውቶቡስ ውስጥ፣ ልጄ ምን ዓይነት ባህሪይ ማሳየት ይጠበቅበታል?
- የማውቃቸውን ምን ዓይነት የባህሪይ ጉዳዮችን ከልጄ ጋር መነጋገር አለብኝ?
- በልጄ ትምህርት ቤት የስነምግባር ፖሊሲዎች እና ደንቦች ምን እንደሚሉ አውቃለሁ ወይ?
- እቤት ውስጥ ስላለ ማንኛውም ችግሮች ከትምህርት ቤቱ ጋር እንዴት ልወያይ እችላለሁ?
- ሁከት መፍጠር ተቀባይነት እንደሌለው ልጄ በሚገባ እንደተረዳው እንዴት አረጋግጣለሁ?
- በመኖሪያ ቤት ቀና የሆነ ባህሪይ እንዲኖር በማድረግ፣ የትምህርት ቤቱን ፖሊሲዎች እና አካሄዶችን እንዴት ለማገዝ እችላለሁ?
- ልጄ የሚያደርገው/የምታደርገው ምርጫዎች ጉዳት ሊፈጥር እንደሚችል መረዳቱን/ቷን እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?
- ልጄ ጉዳትን ባስወገደ መንገዶች በመስራት እንዲጓዝ እንዴት ማበረታታት እና መርዳት እችላለሁ?

### የትምህርት ቤት ሠራተኞችን መጠየቅ

- ልጄ የሚጠበቅበትን/ባትን ባህሪይ ትምህርት ቤቱ እንዴት ይገልጽለታል/ላታል?
- ልጄ የባህሪይ ችግሮች እንዳይኖሩት በምን ዓይነት ሁኔታ ለመጠበቅ/መከላከል እንደምችል ትረዱኛላችሁ? (ማንኛውም የባህሪይ ጉዳዮችን ከትምህርት ቤቱ ጋር መጋራት)
- የስነምግባር ቅጣትን ለማስወገድ ምን እንደሚያስፈልግ፣ በእውነት ልጄ ያውቃል/ታውቃለች?
- ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ-ባህሪይ እንደሚያሳዩ እና ደህንነታቸው እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ ምን እየተደረገ ነው?
- እኔ እንደወላጅነቴ፣ በቤት ውስጥ ምን ዓይነት የስነምግባር ፖሊሲዎችን ማወቅና ማስፈጸም አለብኝ?
- የመልካም ባህሪይ ግልፃ ገብነቶች እና እርዳታዎች (PBIS) ምንድን ነው?
- ማንኛውም ማጋራት የምፈልገውን ነገሮች፣ በእንዴት ያለ መንገድ ማነጋገር ተመራጭ ይሆናል? የስልክ ቁጥር ዝርዝሮች ይኖራሉ?
- ልጄ ቢታገድ፣ ገለልተኛ የሆነ የአቤቱታ ሂደት አለ? የአቤቱታው ሂደት ምን ምን ያስፈልገዋል?

# ማወቅ የሚገባዎ አባባሎች

## አጠቃላይ አባባሎች

- **የመልካም ባህሪይ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ (BIP)**
  ልጁ የማህበረሰብ ችሎታዎቹን እና ባህሪይን እንዲማር የተቀረፀ ዕቅድ፤ መልካም የሆነ ጣልቃ ገብነትን ያካተተ መሆን አለበት

- **የዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (PCSB)**
  በዲሲ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን ስልጣን ይሰጣል፤ ከተሟላ የማመልከቻ ሂደት በኋላ፣ PSCB ስልጣን የሰጣቸውን ትምህርት ቤቶች የበላይ ቁጥጥር እና እርዳታ ይሰጣል

- **የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)**
  በኮሎምብያ ዲስትሪክት የመደበኛ የትምህርት ቤት ዘዴ፤ ማዕከላዊ ባለስልጣን የዲሲ ሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቻንስለር ነው

- **የማግለል የስነምግባር ቅጣት**
  ተማሪውን ከተለመደው የትምህርት ገበታው የሚያስወጣ ወይም የሚያግድ ማንኛውም የስነምግባት ቅጣት፤ ምሳሌዎቹ፣ ማገድ እና በግድ ማስወጣትን ይጨምራል

- **ለየግል የተቀረፀ የትምህርት ዕቅድ (IEP)**
  ልጁ ብቁ በሚሆንበት በጉዳተኝነት ዕቅድ፣ "ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት" ("Free Appropriate Public Education") በመስጠት፣ ልጁ ትርጉም የሚሰጥ እድገት እንዲያሳይ፤ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች ለሚያገኙ ተማሪዎች በIDEA ስር የሆነና ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነ

- **የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (IDEA)**
  በIEP ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች በአንፃራዊነት የሚወሰድ የስነምግባር ቅጣት በፌደራል ሕግ የሚተዳደር፤ በጉዳተኝነታቸው ምክንያት ከተፈጠረ ባህሪይ ጋር በተያያዘ ከሚከሰት ቅጣት ተማሪዎችን ለመጠበቅ ታስቦ የታቀደ

- **የአካባቢ የትምህርት ድርጅት (LEA)**
  በሌሎች ስቴቶች የትምህርት ዲስትሪክቶች እንዳለው ሁሉ፣ የአካባቢው የትምህርት ድርጅት በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሰራል፤ DCPSም LEA በመሆኑ እና እያንዳንዱ ቻርተር ኔትወርኮችም የራሱ LEA ነው።

- **ለውጥ ያስከተለበት መወሰኛ**
  ከተማሪው ጉዳተኝነት እና በይፋ ከሚያሳየው ባህሪይ ጋር በተያያዘ ለስነምግባር ቅጣቱ አስተዋፅዖ ያደረገውን ነገር ግንኙነት ለመገምገም፣ ትምህርት ቤቱ ማግለልን ወይም የሚማርበትን ቦታ ለመቀየር ያሉትን አማራጮች ሲመለከት

# ማወቅ የሚገባዎ አባባሎች

## አጠቃላይ አባባሎች

- **የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)**
  በኮሎምብያ ዲስትሪክት ፍቃድ ያለው የስቴት የትምህርት ድርጅት፣ መረጃን፣ የፖሊሲ መመሪያን፣ እና በትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ የእርዳታ ምንጮችን፣ ለLEA እና ወላጆች ይሰጣል።

  *OSSE ለLEAዎች ለጣልቃ ገብነት ከተጨማሪ እርዳታዎች ጋር በመስራት ትምህርት ቤቶች በስነምግባር ምክንያት ማስወገድን እንዲቀንሱ ለመርዳት ይሰራል።*

- **የመልካም ባህሪይ እርዳታ እና ጣልቃ ገብነት (PBIS)**
  በትምህርት ቤት ውስጥ ለሁሉም ተማሪዎች የባህሪይ እገዛ እና የማህበረሰብ ባህል የመፍጠር ዘዴ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት ስኬታማነትን ለመቀዳጀት የሚደረግ እንቅስቃሴ

- **የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች (PCS)**
  የPCSB ስምምነቶች እንዳፀደቀው፣ ራሱን የቻለ፣ የመማሪያ ገንዘብ የማያስከፍሉ ትምህርት ቤቶች፤ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት በመብትነት ለተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው ሳይሆኑ፣ አብዛኛዎቹ በሎተሪ የሚገኝ የማመልከቻ ሂደትን ማለፍ ያስፈልጋቸዋል

- **አበረታች ወይም መልካም ስነምግባር**
  ግንኙነቶች፣ ማህበራዊ ስሜታዊ የመማር ዘዴ፣ ሃዘኔታ እና ተጠያቂነትን በትምህርት ቤቶች እና ወላጅነትን ማዕከል አድርጎ የተዘጋጀ ቅጣት-አልባ አቀራረቦች እና ቴክኒኮች

- **የትምህርት ቤት ደህንነት እና መልካም አየር የገንዘብ እርዳታ***
  የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE) ትምህርት ቤቶችን በሚከተለው መርዳት ያስፈልገዋል፡
  - የቴክኒካል እርዳታ
  - በከፍተኛ ደረጃ ምርጥ የሆነ ባለሞያዊ እድገት
  - ከሁለተኛ ዲግሪ በኋላ ሰርትፊኬት ፕሮግራሞችን (post-secondary degree certificate programs) እንዲሁም ስለሰቆቃ መረጃ ያለው ስልጠና ሰጪ ሰርቲፊኬት ፕሮግራሞችን ጨምሮ አዘገጃጀትን

  ይህ የገንዘብ እርዳታ እነዚህ ፕሮግራሞች እና ሌሎችንም ትምህርት ቤቱ የሚያስፈልጉትን ማንኛውንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት ለመርዳት ጥቅም ላይ ይውላል።

- **ስለሰቆቃ መረጃ ያላቸው አቀራረቦች**
  በሰቆቃ ባዮሎጂ ዙሪያ ያለውን ስር-ነቀል እውቀት ለማዳበር፣ በሰው ልጅ አሰራር ላይ ያለውን ኃይል፣ እንዲሁም ሰቆቃ-የሚሰማው እና በቶሎ የሚያገግም ለመሆን፤ ሳንይንስተኮር ለሆኑ ሞዴሎች ጥላ የሚል ስያሜ የተሰጠው

- **ምንም ተቀባይነት የሌላቸው (ዜሮ ቶለራንስ) ፖሊሲዎች**
  በማንኛውም ሁኔታ ቢኖን፣ የትምህርት ቤት ሹሞች ቅጣትን ለማስፈጸም የሚያስችላቸው ፖሊሲ ሲሆን፤ የጦር መሣሪያ፣ አልኮል መጠት፣ ወይም ድብድብ ጋር ተያያዥነት ያለው ማገድ ወይም ተማሪዎችን ማስወጣት በተለምዶ የሚጠቀሱ፤ምንም ተቀባይነት የሌላቸው (ዜሮ ቶለራንስ) ፖሊሲዎች ናቸው

*በ2018 በዲሲ ካውንስል የተላለፈው የ'Student Fair Access to School Act' ክፍሎች

በዲስትሪክቱ ውስጥ ስለዚህ መመሪያ ወይም የተማሪ ስነምግባር ጥያቄዎች ይርዎታል? የተማሪዎች ተከራካሪ ቢሮን ያነጋግሩ!

student.advocate@dc.gov | 202-741-4692 | studentadvocate.dc.gov

# ከተማሪ ስነምግባር ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች እና ቢሮዎች

**የስቴት የትምህርት ቦርድ**
202-741-0889
sboe@dc.gov
sboe.dc.gov

**የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እምባ-ጠባቂ ቢሮ**
202-741-0886
om.budsman@dc.gov
educationombudsman.dc.gov

**ከንቲባ**
202-727-2643
eom@dc.gov
mayor.dc.gov

**የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ**
202-727-6439
osse@dc.gov
osse.dc.gov

**የትምህርት ኮሚቴ**
202-724-8061
dccouncil.us
dccouncil.us/committees/education

**የከተማ አስተዳዳሪ**
202-478-9200
oca.eom@dc.gov
oca.dc.gov

**የትምህርት ምክትል ከንቲባ**
202-727-3636
dme@dc.gov
dme.dc.gov

**የሕዝብ ደህንነት እና ፍትህ ምክትል ከንቲባ**
202-724-5400
dmpsj@dc.gov
dmpsj.dc.gov

**የከፍተኛ የኢኮኖሚክ ዕድል ምክትል ከንቲባ**
202-545-3071
dmgeo@dc.gov
dmgeo.dc.gov

**የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ምክትል ከንቲባ**
202-727-7973
dmhhs@dc.gov
dmhhs.dc.gov

# ማወቅ የሚገባዎ ተጨማሪ ቁጥሮች

| | |
|---|---|
| የDCPS የደህንነት ቢሮ | (202) 576-6950 |
| የDCPS እንክብካቤ (ቅሬታ ሰሚ) | (202) 442-5405 |
| የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ | (202) 328-2660 |
| ከተማ-አቀፍ ማንጓጠጥን መከላከያ ፕሮግራም | (202) 727-4559 |
| ሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (MPD) | (202) 727-9099 |
| የሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ (WMATA ፖሊስ) | (202) 962-2121 |
| ለፍትህ እና ትምህርት ተከራካሪዎች | (202) 678-8060 |
| የልጆች ሕግ ማዕከል | (202) 467-4900 |
| UDC የወጣት ጥፋተኞች ሕግ ክሊኒክ | (202) 274-5073 |
| ወደደህንነት ተመላሽ ዲሲ፣ የSchoolTalk ፕሮግራም | (202) 907-6887 |